# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

# የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን

# የሙዚየም ማቋቋሚያ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት አሰጣጥ ረቂቅ መመሪያ

## ቁጥር 764/2013

**ጥቅምት 2005 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

## መግቢያ

- ሙዚየሞች የአንድን አገር ሕዝቦች ባህላዊና ታሪካዊእንዲሁም ኃይማኖታዊ መገለጫየሆኑቅርሶችን በማሰባሰብአየጠበቁና እየተንከባከቡ ለጐብኚዎች፣ ለትምህርት፣ ለጥናትና ምርምር ሥራ እንዲሁም ለመዝናኛነት እንዲውሉ የሚያደርጉት አስተዋጽአ ከፍተኛ ነው፡፡ ሙዚየሞች በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ኩነቶችን ያስተናግዳሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በቋሚነት ቅርሶችን ከማቅረብ በተጨማሪ በተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ አዝናኝና ትምህርት ሰጭ ጊዜያዊ ኤግዚቢሽኖች በማዘጋጀት፣ የባህል መለዋወጫና የጋራ መግባቢያ መድረኮች በመሆን እንዲሁም ወቅታዊ አገር አቀፍና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያቀርባሉ፡፡ በመሆኑም በሀገራችን የሚገኙና ወደፊት የሚቋቋሙ ሙዚየሞች ከላይ የተገለፁትን እውነቶች በሚገባ እንዲያካሂዱና ዘመናዊ አሠራሮችን ተከትለው በመልካም የውድድር መድረክ ውስጥ በመሆን ዓለም ከደረሰበት ዘመናዊ አሠራር ጋር እንዲራመዱ ለማድረግና በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣንና በሀገሪቱ በሚገኙ የሙዚየም ባለይዞታዎች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ህጋዊና ተመጋጋቢ የሥራ ግንኙነት ግልፅ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ፣ ሙዚየሞቸም ተወዳዳሪ ሆነው ለሀገሪቱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ እድገት የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ ለማስቻል በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ 209/1992 አንቀጽ 15 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## አውጭው ባለስልጣን

የባህልና ቱሪዝምሚኒስቴር በቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀጽ 15 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሙዚየም ማቋቋሚያ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት አሰጣጥ ረቂቅ መመሪያ" ቁጥር 764/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ትርጓሜ

በአዋጅ ቁጥር 209/92 አንቀጽ 3 የተሰጠው ትርጓሜ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የኢትኖግራፊ ሙዚየም" ማለት የብሔር ብሐረሰቦችንና ህዝቦችን ወይም የአንድን ብሔርባህላዊ እሴቶች የሚገልፁቅርሶች በማሰባሰብ ለእይታ የሚያቀርብ ሙዚየም ነው፡፡

2. "የስነጥበብ ሙዚየም" ማለት የስዕል፣ ቅርፃ ቅርፅ ሌሎችንም የፈጠራ ሥራዎች ለማሳየት የተቋቋመ ሙዚየም ነው፡፡

3. "የታሪካዊዘመን ሙዚየም" ማለት የታሪካዊ ቅርሶችን አሰባስቦ የሚያሳይ ሙዚየም ነው፡፡
4. "የአርኪዎሎጂ ሙዚየም" ማለት የአርኪዎሎጂ ቅርሶችን አሰባስቦ የሚያሳይ ሙዚየም ነው፡፡

5. "የአጠቃላይ ስብስብ ሙዚየም" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የስብስብ አይነቶችን ማለትም የኢትኖግራፊ፣ የስነ ጥበብ፣ የታሪክ ዘመን፣ የአርኪዎሎጂስብስቦችያሉት ሆኖ እነዚህን ለእይታ የሚያቀርብ ማለት ነው፡፡

6. "በኃይማኖት ተቋማት የተመሠረተ ሙዚየም" ማለት፣ በኃይማኖት ተቋማት ባለይዞታነት ተመስርቶ የተቋቋመ ሙዚየም ነው፡፡

7. "የመታሰቢያ ሙዚየም" ማለት አንድን ክስተት ወይም ታሪክ ወይም፣የግለሰብ/የግለሰቦችን ታሪክ ወይም ሂደት ለማስታወስ የተቋቋመ ሙዚየም ነው፡፡

8. "የግል ሙዚየም" ማለት በግለሰብ ባለይዞታነት የሚተዳደር ሙዚየም ነው፡፡

9. "የትርኢት ገላጭ ባለሙያ" ማለትበሙዚየም የተዘጋጀውን ኤግዚቢሽን ለመግለጽ ወይም ለማስረዳትየሰለጠነ ባለሙያ ነው፡፡

10.. ``የትርኢት ዝግጅት ባለሙያ" ማለት በሙዚየም ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ኤግዚቢሽኖችን የሚያዘጋጅባለሙያ ነው፡

11. "የሙዚየም ባለይዞታ" ማለት ህጋዊና ሙያዊ በሆነ መንገድ ሙዚየም አቋቁሞየሚያስተዳድር አካል ማለት ነው፡፡

12. “የሙዚየም ደረጃ” ማለት ሙዚየሞች ባላቸው ስብስብ ዓይነት በአደረጃጀታቸው፣ በሰው ኃይል ስብጥራቸውየሚሰጣቸው ደረጃ ማለት ነው፡፡

13. “የሙዚየም አይነት” ማለት ሙዚየሞች በስብስባቸውና በሚሰጡት አገልግሎት ወይምበባለይዞታነትወይም በተደራጀበት ቦታ የሚለዩበት ወይምየሚታወቁበት ነው፡፡

14. “ቅድመእውቅና ያገኙ ሙዚየሞች” ማለት ሙሉ እውቅና ከማግኘታቸው አስቀድሞ በከፊል መስፈርቶችን ማሟላታቸው ሲረጋገጥየሚሰጣቸው የእውቅናዓይነት ነው፡፡

15. “እውቅና ያገኙ ሙዚየሞች” ማለት በየደረጃው የተቀመጡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉማሟላታቸው ሲረጋገጥ የሚሰጥ እውቅና ነው፡፡

16. “በሙዚየምመልክ የተደራጀ ተቋም” ማለት ቅርሶችን ወይም ልዩ ልዩ መስተጋብሮችንበቋሚነትለማሳየት የተቋቋመ ድርጅት ማለት ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ቀደም ብለው በሀገሪቱ በተቋቋሙ ሙዚየሞችናወደፊት በሚቋቁሙ ሙዘየሞች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የሙዚየም አደረጃጀት

## 5. ሙዚየም ስለማቋቋም

1. ሙዚየም በግል ወይምበማህበር ወይም በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም በኃይማኖት ተቋማት ሊቋቋም ይችላል፡፡

2. ሙዚየም ለማቋቋም ከባለሥልጣኑ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

3. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተቋቋሙ ሙዚየሞች ፀንተው ይቆያሉ፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀው ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከተውን መመዘኛ የማሟላት ግዴታ አለባቸው፡፡

## 6. የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የሙዚየም ዓይነቶችና ደረጃዎች

1. የሚቋቋሙ የሙዚየም አይነቶች
   ሀ. የኢትኖግራፊ ሙዚየም
   ለ. የሥነ ጥበብ ሙዚየም
   ሐ. የታሪክ ዘመን ሙዚየም
   መ. የአርኪዎሎጂ ሙዚየም
   በ. የሰው ዘር ምንጭ ሙዚየም
   ተ. የተፈጥሮ ቅርስ ሙዚየም
   ቸ. ልዩ ሙዚየሞች

ሠ. አጠቃላይ ሙዚየም
ረ. ወታደራዊ ሙዚየም
ሰ. የፖስታ ሙዚየም
ሸ. የኃይማኖታዊ ተቋማት ሙዚየም
ቀ. የመታሰቢያ ሙዚየም
ከ. ኦፕን ኤር ሙዚየም
አ. በሙዚየም መልክ የተደራጀ ተቋም

2. የማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የሙዚየም ደረጃዎች
   ሀ. ደረጃ 1
   ለ. ደረጃ 2
   ሐ. ደረጃ 3

3. የሙያና የብቃት ማረጋገጫ እንደ ሙዚየሞቹ የእድገት ደረጃ በመጀመሪያ በዚህ መመሪያ ውስጥ ለተጠየቀው የሙዚየም ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት ሰባ አምስት በመቶ ሲያሟላ የቅድመ ዕውቅና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት በመቀጠልም ለ6ወር በሚሰጠው የቆይታ ጊዜና ግምገማ መሠረት የሙሉ ዕውቅና የሚሰጥ ይሆናል፡፡

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከተዘረዘሩት የሙዚየም አይነቶች መሠረት በማድረግ ፍቃድ ይሰጣል፡፡

5. የሰውዘርአመጣጥን የሚያሳይ ሙዚየም ወይም የፖሊዮንቶሎጂና የፖሊዮአንትሮፖሎጂ አርኪዎሎጂ ሙዚየሞች በመንግሥት አካላት ብቻ ይቋቋማሉ፡፡

6. ይህ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ሙዚየም ለሚያቋቁሙ አካላት ፍቃድ መስጠት ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሶስት
## መመዘኛዎች

### 7.የኢትኖግራፊሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. ደረጃ 1 የኢትኖግራፊ ሙዚየም
   ሀ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ ከ300 ስኩዌር ሜትር ያላነሰ መሬት ላይ ያረፈ

   ሆኖ አሠራሩ የአገሪቱን ወይም የአካባቢውን ባህል የሚያንፀባርቅ መሆንይኖርበታል፡፡

   ለ. ሙዚየሙ መያዝ ያለበት የቅርሶች ስብስብ ከ5000 ያላነሰና ብዛቱና ዓይነቱ

   የአገሪቱን ወይም የሚያቋቁመውን ክልል ባህል የሚወክል ሆኖ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡

   ሐ. ስብስቡ የብሔር ብሔረሰቦችንና የኃይማኖት እኩልነትየሚያከብርና የተሟላ መረጃ

   ሊኖረው ይገባል፡፡

   መ. ቅርሶቹ የሚታዩበት ሥፍራ በማሳያ ግብዓቶች ማለትም በሾው ኬዝ፣ፓናል፣

   መብራቶችና ለአውደ ርዕይ አገልግሎት በሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችየተሟላመሆን አለበት፡፡

ሠ. ሙዚየሙ ለጐብኚዎች አመቺ በሆነ፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት ቅርበትያለው፣ ቅጥርግቢው

ለመኪና ማቆሚያ በቂ ስፍራ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

ረ. ሙዚየሙ የሰለጠነ የቅርስ እንክብካቤና ጥገና፣ የቅርስ አሰባሳቢ፣ ቢያንስ አራት የትርኢት ገላጭ፣ ሁለት የሴኩሪቲ ባለሙያዎች ያለው፣

ሰ.የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ አስተማማኝ የጥበቃ ቡድን፣ የእሳትመከላከያ የአደጋ ጊዜ

ማስጠንቀቂያ አላርም፣ የመውጫ በርና ዘመናዊ የእሳትማጥፊያያለው፣

ሸ. የቅርስ ክምችት ክፍል፣ ላቦራቶሪ ክፍል፣ የኬሚካልና የቅርስ ጥገናክፍል ያለው፣

ቀ. ከሀያ ያላነሱ የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያሉት እነዚህም የመረጃ ዴስክ፣የትኬት መቁረጫ፣ የእንግዳ ማረፊያ፣ የቋሚና ጊዜያዊኤግዚቢሽን አዳራሽ፣የኦዲዮቪዥዋል፣የደህንነት ጥበቃ ክፍል፣ ቤተመፃሕፍት ክፍልያለው ፣

በ. ሙዚየሙ ስለ አጠቃላይ አገልግሎቱ ማለትም የመግቢያ ዋጋ ለአዋቂ፣ለተማሪ፣ ለውጭ ዜጐች፣

በሰሌዳ ያሳወቀ እንዲሁም ስለ እያንዳንዱትርኢት ክፍል በቂ መግለጫና አቅጣጫ ጠቋሚ ያዘጋጀ፣

ተ. ወለሉ ከድምፅ፣ ከንዝረት፣ ከመንሸራረት የሚከላከልና ቀለሙ ለእይታየማይረብሽ የሆነ፣

ቸ. ሙዚየሙ በዳይሬክተር /ሥራ አስኪያጅ የሚመራ፣

ኣ. በፆታ የተከፋፈለ የመፀዳጃ ቤት ያለው፣

ከ. የራሱ የሆነ ድረ ገጽ፣ ዳታ ቤዝና የህትመት ውጤቶች ያለው፣

ወ. ዘመናዊ የቅርስ አመዘጋገብና የስብስብ ፖሊሲ ያለው፡፡

ዐ. በቂ የአየርማስገቢያያለው፣

ዘ. ሠራተኞችናጐብኚዎችየሚስተናገዱበትካፍቴሪያያለው

ዠ. ለአካል ጉዳተኞችአመቺየሆነ፣

## 2. ደረጃ 2የኢትኖግራፊ ሙዚየም

ሀ. ለሙዚየሙ የሚሆነው ህንፃ ከ200 ስኩዌር ሜትር ያላነሰ መሬት ላይ ያረፈሆኖ

አሠራሩ የአገሪቱን ባህል የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፡፡

ለ. ሙዚየሙ መያዝ ያለበት የቅርሶች ስብስብ ከ 3000 ያላነሰና ብዛቱናአይነቱ የአገሪቱን ወይም የሚቋቋምበትን ክልል ባህል የሚወክል ሆኖ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

ሐ.የቅርሶችን ስብስብ የብሔር ብሔረሰቦችንና የኃይማኖትን እኩልነትየሚያከብርና የተሟላ መረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

መ. ቅርሶቹ የሚታዩበት ስፍራ በማሣያ ግብዓቶች ማለትም በሾው ኬዝ፣ ፓናል፣ መብራቶችና ለዓውደ ርዕይ  አገልግሎት በማያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተሟላመሆን ይኖርበታል፡፡

ሠ. ሙዚየሙ ለጐብኝዎት አመቺ በሆነ ሥፍራ የሚገኝ ሆኖ ለትራንስፖርት አገልግሎትቅርበት

ያለውና ቅጥር ግቢው በቂ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ያለው፣

ረ. ሙዚየሙ የሰለጠኑ የሙዚየም አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች የትርኢት ገላጭ፣የቅርስ አሰባሳቢ

ባለሙያዎች ያለው፣

ሰ. የቅርሶችን ደህንነት ለመጠበቅ አስተማማኝ የጥበቃ ቡድንና የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎችን ያሟላ፣

ሸ. ከ15 ያላነሱ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያሉት እነዚህም የመረጃ ዴስክ፣ የትኬትመቁረጫ፣ የእንግዳ መቀበያ፣ የደህንነት ጥበቃና ሌሎችየአስተዳደር አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያሉት፣

ቀ. የቅርስ ክምችት ክፍል ያለው

በ.ሙዚየሙ ከቅርስ አስተዳደር ጋር ተያያዥነት ባለው ሙያ በሰለጠነዳይሬክተር/ሥራአስኪያጅ

የሚመራ፣

ተ.የሙዚየሙወለል ከንዝረት፣ከድምፅ፣ከማንሸራተት ነፃ የሆነና ለእይታ የማይረብሽ፣

ቸ.  በፆታ የተከፋፈለ መፀዳጃ ቤት ያለው፡፡

ኀ. የራሱ የሆነ ድረ ገጽ፣ ዳታ ቤዝና የህትመት ውጤቶች ያለው፣

ነ. ዘመናዊ የቅርስ አመዘጋገብና የስብስብ ፖሊሲ ያለው፡፡

ኘ. በቂ የአየርማስገቢያያለው፣

አ.  ሠራተኞችናጐብኚዎችየሚስተናገዱበትካፍቴሪያያለው

ከ.  ለአካል ጉዳተኞችአመቺየሆነ፣

## 3. ደረጃ 3 የኢትኖግራፊ ሙዚየም

ሀ. ለሙዚየሙ የሚሆን ህንፃ ከ100 ስኩዌር ሜትር ያላነሰ መሬትላይ ያረፈ፣

ለ. ሙዚየሙ መያዝ ያለበት የቅርሶች ስብስብ ከ 1000 ያላነሰና ብዛቱና ዓይነቱ የአገሪቱን

ወይም የሚቋቋምበትን ክልል ባህል የሚወክል ሆኖ ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

ሐ. የቅርሶቹ ስብስብ የብሔር ብሔረሰቦችንና የኃይማኖቶችን እኩልነት የሚያከብርና የተሟላ መረጃ ሊኖረው

ይገባል፡፡

መ. ሙዚየሙ ለአውደ ርዕይ ለሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማለትም በሾው ኬዝ፣ ፓናል፣ፔዴስታሎች የተሟላ ሊሆን

ይገባል፡፡

ሠ. ሙዚየሙ ለደህንነት አስተማማኝና ለትራንስፖርት አመቺ በሆነ መንገድ ሥፍራ መገኘትአለበት፡፡

ረ. ከስምንት ያላነሱ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያለው ማለትምየትኬት መቁረጫ

የእንግዳ መቀበያ፣ የጥበቃ ክፍል፣ የአስተዳደር አገልግሎት መስጫ፣ የቅርስ ከምችት ክፍል ያለው፣

ሰ. የትርኢት ገላጭ ባለሙያ ያለው፣

ሸ. በዖታ የተከፋፈለ መፀዳጃ ቤት ያለው፣

ቀ. የራሱ የሆነ ድረ ገጽ፣ ዳታ ቤዝና የህትመት ውጤቶች ያለው፣

በ. ዘመናዊ የቅርስ አመዘጋገብና የስብስብ ፖሊሲ ያለው፡፡

ተ. በቂ የአየርማስገቢያያለው፣

ቸ. ሠራተኞችናጐብኚዎችየሚስተናገዱበትካፍቴሪያያለው

ኀ. ለአካል ጉዳተኞችአመቺየሆነ፣

## 8. የስነ ጥበብ ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች

### 1. ደረጃ 1 የስነ ጥበብ ሙዘየም

ከላይ ከአንቀጽ 7 በንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ" እስከ "ኀ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትንም መሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ከ250 ያላነሱ ጥንተዊና ዘመናዊ የስነ ጥበብ ቅርሶች ስብስብ ያለው፣

ለ. በስነጥበብ ሙያ የሰለጠኑ 3 ባለሙያዎች ያሉት፣

ሐ. የቅርፃ ቅርፅ ወይም ሃውልቶት ማስቀመጫ ፔዳስታሎች ያሉት፣

### 2 ደረጃ2 የስነ ጥበብ ሙዚየም

በአንቀጽ 7 በንዑስ አንቀጽ "2"ከፊደል “ሀ” እስከ "ከ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትንም ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ከ175 ያላነሱ ጥንታዊና ዘመናዊ የስነ ጥበብ ቅርሶት ስብስብ ያለው፣

ለ. በስነጥበብ የሰለጠነ ቢያንስ 2 ባለሙያ ያለው ፣

ሐ. የቅርፃ ቅርፅ ወይም ሃውልቶች ማስቀመጫ ፔድስታሎች ያሉት፣

### 3. ደረጃ 3 የስነጥበብ ሙዚየም

በአንቀጽ 7 በንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል "ሀ" እስከ "ኀ" የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትንም ማሟላት አለባቸው::

ሀ. ከ100 ያላነሱ ጥንታዊና ዘመናዊ የስነጥበብ ቅርሶች ስብስብ ያለው፣

ለ. በስነጥበብ የለጠነ ቢያንስ 1 ባለሙያ ያለው፣

ሐ. ለቅርፃ ቅርፅ ሥራዎች የራሱ የሆነ ማስቀመጫ ያለው ፣

## 9. የታሪክ ዘመን ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች

### 1. ደረጃ1 የታሪክ ዘመን ሙዚየም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ሀ እስከ ዠ የተዘረዘሩት መስፈርቶችእንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው::

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዛቸው ቅርሶች የኢትዮጵያ ብሔሮችንና ብሔረሰቦችን ትክክለኛ ታሪክ በማስረጃ የያዘ፣

ለ. ቅርሶቹ የተለያየ ዘመን ታሪክ የሚያሳዩ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃየሚሰጡ መሆን ይገባቸዋል::

ሐ. ለአልባሳት ቅርሶች፣ ለጥንታዊ መጽሐፍት የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሳቁስ ለይቶ ያዘጋጀ፣

መ. ከ3 በላይ የሰለጠኑ የታሪክ ዘመን ባለሙያዎት ያሉት

### 2. ደረጃ 2 የታሪክ ዘመን መዚየም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ሀ እስከ ከ የተዘረዘሩት መስፈርቶ እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው::

ሀ. ሙዚየሙ የሚይዘቸው ቅርሶች የኢትዩጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦችን ትክክለኛ ታሪክ ከነማስረጃው የያዘ፣

ለ. ቅርሶቹ የተለያየ ዘመን ታሪክን የሚያሳዩ ጉዳት ያልደረሰባቸው በትክክል የሚፈለገውን መረጃ የሚሰጠ መሆን ይገባቸዋል::

ሐ. ለአልባሳት ቅርሶች፣ ለጥንታዊ መጽሐፍት የሚሆን ልዩ ልዩ የማሳያ ቁሰቁሶች ለይቶያዘጋጀ::

መ. ከሁለትየማያንሱ የታሪክ ዘመን ባለሙያዎች ያሉት::

### 3.ደረጃ 3የታሪክዘመንሙዚየም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል “ሀ” እስከ “ኀ” የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው::

ሀ. ሙዚየም የሚይዛቸው ቅርሶች የኢትዮጵጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦችን ትክክለኛ ታሪክ ከነማስረጃው መያዝ አለባቸው ፣

ለ. ለታሪካዊ ስብስቦች አመቺ የሆነ የዐውደ ርዕይ ማሳያ ቁሳቁሶች ያለው ፣

ሐ. በቅርስ ወይም በታሪክ ዘመን የሰለጠነ ቢያንስ አንድ ባለሙያ ያለው ፣

## 10. የአርኪዎሎጂ ሙዚየም ለማቋቋም የሚያበቁ መስፈርቶች

### 1. ደረጃ 1 የአርኪዎሎጂ ሙዚየም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ሀ እስከ ዠ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ.ሙዚየሙየሚይዛቸውየአርኪዎሎጂቅርሶችትክክለኛታሪክማስረጃየያዘ፣(በቁፋሮየተገኙቅርሶችምጥናትናምርምርተካሂዶባ ቸውትክክለኛነታቸውየተረጋገጠ መሆንይኖርበታል)

ለ. ቅርሶቹጉዳትያልደረሰባቸውበትክክልየሚፈለገውንመረጃየሚሰጡመሆንይገባቸዋል፡፡

ሐ. ለቅርሶችየሚሆንልዩልዩየማሳያቁሳቁስለይቶያዘጋጀ፣

መ. ከ3 በላይየሰለጠኑየአርኪዎሎጂባለሙያዎችያሉት

### 2. ደረጃ 2 የአርኪዎሎጂመዚየም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ሀ እስከ ከ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙየሚይዛቸውየአርኪዎሎጂ ቅርሶችትክክለኛታሪክማስረጃየያዘ፣ (በቁፋሮየተገኙቅርሶችምጥናትናምርምርተካሂዶባቸውትክክለኛነታቸውየተረጋገጠ መሆንይኖርበታል)

ለ. ቅርሶቹጉዳትያልደረሰባቸውበትክክልየሚፈለገውንመረጃየሚሰጡመሆንይገባቸዋል፡፡

ሐ. ለቅርሶችየሚሆንልዩልዩየማሳያቁሳቁስለይቶያዘጋጀ፣

መ. ከሁለት የማያንሱ የሰለጠኑ የአርኪዎሎጂ ባለሙያዎች ያሉት,

### 3. ደረጃ3የአርኪዎሎጂመዚየም

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ሀ እስከ ኀ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪነት የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ.ሙዚየሙየሚይዛቸውየአርኪዎሎጂ ቅርሶችትክክለኛታሪክማስረጃየያዘ፣(በቁፋሮየተገኙቅርሶችምጥናትናምርምርተካ ሂዶባቸውትክክለኛነታቸውየተረጋገጠ መሆንይኖርበታል)

ለ፣ ቅርሶቹጉዳትያልደረሰባቸውበትክክልየሚፈለገውንመረጃየሚሰጡመሆንይገባቸዋል፡፡

ሐ. ለቅርሶችየሚሆንልዩልዩየማሳያቁሳቁስለይቶያዘጋጀ፣

መ. በአርኪዎሎጂመስክ የሰለጠነ ቢያንስ አንድ ባለሙያ ያለው ፣

## 11. አጠቃላይሙዚየምለማቋቋምየሚበቁመመዘኛዎች

### 1.ደረጃ 1 ከፍተኛ አጠቃላይ ሙዚየም

ከላይ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ሀ እስከ ዠ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ ቢያንስ አራትየስብስብ ዓይነቶችን መያዝ ይኖርበታል

ለ. ለእይታ የሚቀርቡት ቅርሶች እንደ አይነታቸው የየራሳቸው ክፍሎች ለየብቻ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

ሐ.የሙዚየሙ የትርኢት ክፍሎች የራሳቸው የክፍል መግለጫ የተዘጋጀላቸው መሆን አለበት፡፡

መ.በሙዚየም፣በታሪክ፣ በአንትሮፖሎጂ፣ በስነጥበብና በዲዛይን በአርኪዎሎጂ ወይም በተመሳሰይየትምህርት መስክ የሰለጠነ ባለሙያ ያለው መሆን አለበት፡፡

## 2 ደረጃ 2 አጠቃላይ ሙዚየም

በአንቀጽ 7 በንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ሀ እስከ ከ የተዘረዘሩት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. ሙዚየሙ ቢያንስ 3 ዓይነት የስብስብ ዓይነቶችን መያዝ ይኖርበታል

ለ. ለእይታ የሚቀርቡት ቅርሶች እንደ አይነታቸው የየራሳቸው ክፍሎች ለብቻ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

ሐ. የሙዚየም የትርኢት ክፍሎች የየራሳቸው የክፍል መግለጫ የተዘጋጀላቸው መሆን አለበት፡፡

መ. ሙዚየሙ የሰለጠኑ የታሪክ፣ የአንትሮፖሎጂና የሥነ ጥበብና የትርኢት አዘጋጅ ባለሙያዎች ሊኖረው ይገባል፡፡

## 3.ደረጃ 3አጠቃላይሙዚየም

በአንቀጽ 7 በንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል "ሀ" እስከ "ኀ"የተዘረዘሩት መስፈርቶት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትንም ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. ሙዚየሙ ቢያንስ ሰ2 ዓይነት የስብስብ አይነቶች ማደራጀት አለበት፡፡

ለ. ለእይታ የሚቀርቡ ቅርሶች የየራሳቸው ክፍሎች ኖሯቸው መግለጫ የተዘጋጀላቸው

ሐ. ሙዚየሙ ቢያንስ በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ በታሪክ፣ ወይም አንትሮፖሎጂ፣ ወይም ሥነጥበብና ዲዛይን ወይም ተመሳሳይ ወዘተ.../ሁለት የሰለጠኑ የትርኢት ባለሙያዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

## 12. ሌሎች የሙዚየም ዓይነቶችን በተመለከተ

1. በዚህ ረቂቅ መመሪያ በአንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 1 ሥር የተዘረዘሩት የሙዚየም ዓይነቶች አንቀጽ 7 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሲያሟሉ የደረጃውን የምሥክር ወረቀት ያገኛሉ፡፡

2. በዚሁ አንቀጽ ተራ ቁጥር 13 የጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሙዚየሞች ደረጃቸበሚያቀርቡትመረጃ መሠረት ደረጃቸውን ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>

# <u>መብትና ግዴታዎች</u>

## 1. <u>በበ. የሙዚየም ባለይዞታ መብት</u>

ሀ. ቅርሶችን በውርስ ወይም በውሰት ወይም በግዥ ወይም በጥናትና ምርምር ወይም በአደራ ወይም በሌላ

ህጋዊ መንገድ የማሰባሰብ፣

ለ. ከሚዘጋጀው ኤግዚቢሽን ወይም የመዚየም አገልግሎት ወይም ከጥናትና ምርምር አገልግሎትክፍያ የማግኘት

ሐ. ሙዚየሙን የማሻሻል ወይም ተጨማሪ ቅርሶችን የመሰብሰብ ወይም ከሙዚየም አገልግሎት ጋርተያያዥ

በሆነመልኩ ጥናት፣ ምርምር የማድረግ ሲምፖዚየም፣ ጊዜያዊ ኤግዚቢሽንየማዘጋጀት፣

መ ለሙዚየሙ እድገት የማቀድ፣በዚሁ መሠረት የመንቀሳቀስ፣ ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችንየመክፈት፣

ከሚመለተው መሥሪያ ቤት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሙያዊ ድጋፍየማግኘት፣

ሠ. የሙዚየሙን ደረጃ የማሻሻል፣ ከአንድ በላይ ሙዚየም የማቋቋም፣

## 14. የሙዚየም ባለይዞታ ግዴታ

ሀ. ቅርስን አስመልክቶ የወጡ ህጎችንና ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች የማክበር፣

ለ. ሙዚየሙ ሲዘጋ ወይም አገልግሎት ሲያቋርጥ ወይም ቅርሱን ለተመሳሳይ ድርጅት

ሲያስተላልፍ ወይም በማናቸውም ሁኔታ ሲዘጋ በቅድሚያ ለባለስልጣኑ በፅሑፍ የማሳወቅ፣

ሐ. ቅርሶችን ለኤግዚቢሽን ሲያንቀሳቅስ ኢንሹራንስ የመግባት፣

መ. የባለሥልጣኑባለሙያዎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለሚያደርጉት ቁጥጥር የመተባበር፣

ሠ. በሙዚየሙ ውስጥ ያሉ ቅርሶችን በሙሉ መረጃ የያዘ ሰነድ የማዘጋጀት የማደራጀት፣

ረ. በሙዚየሙ ውስጥ ያለውን የቅርስ ዝርዝር በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ፣

ሰ. የተሰጠውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ከባለሥልጣን መ/ቤቱ እውቅና ውጭ ለ3ኛ ወገን

አሳልፎ አለመስጠት፣

ሸ. በይዞታው ሥር ያሉት ቅርሶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ፣

ቀ. የሙዚየሙን የብቃት ማረገገጫ የምሥክር ወረቀት በየሁለት ዓመቱ የማደስ፣

በ. ለሀገራዊ ጉዳዮችቅርሶችሲፈለጉ የመተባበር

ተ. የቅርስ ስብስብ ፖሊሲ የማዘጋጀት፣

ቸ. የሙዚየሙ ባለይዞታ ንብረት የሆኑ ቅርሶች የሀገሪቱ ሀብት በመሆናቸው ያለባለስልጣኑፍቃድ በማንኛውም

ሁኔታ ከሀገር ማስወጣት የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል አምስት

## ፈቃድ ስለመስጠት፣ ስለማደስና መሰረዝ

## 15. . የሙዚየም አገልግሎት የሙያና ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድለማግኘትየሚቀርብ ማመልከቻና መሟላት ያለባቸው ሌሎች ማስረጃዎች

1. ከባለሥልጣኑ የሙዚየም የማቋቋሚያ፣የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከቻ በጽሑፍ ለባለሥልጣኑ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ከማመልከቻው ጋርምየሚከተሉትን ማስረጃዎች ማያያዝ ይኖርበታል፡፡

   ሀ. ሙዚየሙን ለማቋቋም የጠየቀው አካል ሙሉ ስም፣

   ለ. ሙዚየም የሚቋቋምበት /የተቋቋመበት ቦታ ሙሉ አድራሻ፣

   ሐ. ሙዚየሙ የያዛቸው ወይም የሚይዛቸው የቅርሶች ዓይነትና መጠን

   መ. የቅርሶች ዝርዝርና ያሉበት ወቅታዊ ሁኔታ

   ሠ. ለሙዚየምነት የተመረጠው ወይም የሚያገለግለው የህንፃ ዓየነት ስፋትና የክፍሎች ብዛት

   ወይም ኘላን

   ረ. የሙዚየሙ ተደራሽነት

   ሰ. የሙዚየሙ መቋቋም ለህብረተሰቡና ለሀገሪቱ ያለው ፋይዳ

   ሸ. ሙዚየሙ ያለው የሰው ኃይል ብዛትና የስልጠና ዓይነት

   ቀ. ሙዚየሙ ያሉት የማሳያ ግብዓቶችና የሀብት መጠን እና ሥራ ማስኬጃ መካተት

   ይኖርባቸዋል፡፡

2. ፍቃድ ለማግኘት በጽሑፍ ከሚቀርብ ማመልከቻ በተጨማሪ ከላይ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል "ሀ; እስከ "ቀ; የተጠቀሱትንና ሌሎች ይጠቅሙኛል የተባሉ መረጃዎችን በሲዲ በሀርድ ኮፒ ከማመልከቻው ጋር ማስገባት ይኖርበታል፡፡

3. የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ከቀረበው ማመልከቻ በተጨማሪ በአካል በመገኘት ለሚያደርጉት የማረጋገጥ ሂደት መረጃዎችን በመስጠት ጠያቂው አካል መተባበር አለበት፡፡

4. አንድ የሙዚየም ፈቃድ ጠያቂ ጉዳዩን የሚያስረዳ ከአንድ ገጽ ያልበለጠና ማመልከቻና ሌሎች ማስረጃዎች ለባለስልጣኑ በአካል በመቅረብ ወይም በፖስታ አድራሻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

5. የሙዚየም ማቋቋሚያ ፈቃድ ጠያቂው ለሚመለከተው ክፍል ከተመራለት በኋላ ለዚህ የተዘጋጀውን ቅጽ ይሞላል፡፡ ይህም ቅጽ በአንቀጽ 10 በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር ከፊደል ሀ እስከ ቀ የተጠቀሱትን ያካትታል፡፡

6. የተሞላውን ቅጽ በመፈረምና ከቀረበው ማስረጃ ጋር በማያያዝ ይመልሳል፡፡

7. ማንኛውም የባለሠለጣኑ የሙያና ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት የሚመጣ የሙዚየም በለይዞታ ማመልከቻ ካስገባ በኋላ ፎርም ለማግኘት ብር 100/አንድ መቶ ብር/ መክፈል ይኖርበታል፡፡

8. ለቅድመ እውቅና የምሥክር ወረቀት ብር 100/አንድ መቶ/ ለሙሉ እውቅና 200/ሁለት መቶ ብር/ ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የአገልግሎት ክፍያ መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡

16. **. የሙዚየም አገልግሎት የሙያና ብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ግምገማና ፈቃድ አሰጣጥ**

1. በግምገማ የቀረበ ማመልከቻና ማስረጃ ያልተሟላ ሆኖ ከተገኘ ጥያቄውን ላቀረበው አካል መጠይቁን አሟልቶ ወይም አስተካክሎ እንዲያቀርብ በባለሥለጣኑ ጽ/ቤት በኩል ይገለጽለታል፡፡ ደብዳቤው በተፃፈ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስተካክሎ ወይም አሟልቶ ካልቀረበ ጥያቄው ይሰረዛል፡፡
2. ለግምገማ የቀረበው ማመልከቻ ማስረጃዎች እንዲሁም የባለሙያዎች የመስክ አስተያየት በተሟላ ሁኔታ መስፈርቶቹን የሚያሟላ መሆኑ ከተረጋገጠ በሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተረጋግጦ በባለስልጣኑ ማናጅመንት ሲወሰን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ፈቃዱ ይሰጣል፡፡
3. የሙዚየም ማቋቋሚያ የሙያና የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት የሚያገለግለው ለሁለት ዓመት ይሆንና በየሁለት ዓመቱ መታደስ ይኖርበታል፡፡ ክፍያውም በአንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 8 መሠረት ይፈፀማል፡፡ አገልግሎቱ የተቋረጠ ሙዚየምም ፈቃዱን ለባለስልጣኑ ይመልሳል፡፡
4. በየጊዜው የሙዚየምን ደረጃና ዓይነት ለማሻሻል የሚፈልጉ የሙዚየም ባለይዞታዎች በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሠረት የሚስተናገዱና ፍቃድ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

17. **. ሙዚየም ለሚያቋቋሙና ላቋቋሙ የሱፐርቪዥንና አገልግሎት ስለመስጠት**

1. ሙዚየም ለሚያቋቁሙና ላቋቋሙ በባለስልጣኑ ባለሙያዎች አማካኝነት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሙያዊ ድጋፍ ከትትልና ግምገማ ያካሂዳል፡፡
2. ከባለስልጣኑ ሙዘየም ለማቋቁምና የኤግዚቢሽን ዝግጅትን አስመልክቶ ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ የሚጠይቅ አካል የቀጣዩ ዓመት በጀት ከመያዙ ከአንድ ወር በፊት በማመልከቻ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. የባለስልጣኑ ባለሙያዎችን እገዛ በአስቸኳይ የሚፈልግ ከሆነ ጠያቂው አካል በሙሉ ወጭውን በመሸፈን የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችን በማስፈቀድ ሊጠቀም ይችላል፡፡
4. የባለሥልጣኑ መ/ቤት ባለሙያዎች የሙዚየሞችን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ ወይም ለጥናት ወይም ለብቃት ማረጋገጫ የሱፐርቪዥን አገልግሎት በተመለከተ በተለያየ ጊዜ ወደ ሙዚየም በመምጣት ትብብር ሲጠይቁ መረጃ በመስጠት ትብብር ማደረግ ይኖርበታል፡፡
5. በሱፐርቪዥን አገልግሎት ወቅት የዲስፕሌይ ሁኔታ፣ የማሳያ ግብዓቶች ለጐብኝዎች የሚሰጥ አገልግሎት፣ መብራቶች፣ የቅርሶች ደህንነት የባለሙያዎች ብቃትና አጠቃላይ ሂደቶች ተገምግመው የሚሻሻሉበት ሁኔታ ሀሳብ ይቀርባል፡፡

18. **. የምሥክር ወረቀት ስለማደስና ስለመሠረዝ**

የሙዚየም የሙያና የብቃት ማረጋገጫ ከባለሥለጣኑ ያገኘ ማንኛውም ግለሰብ ፍቃዱን በየሁለት ዓመቱ ማደስ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለሥለጣኑ ፍቃዱ የተሰጠው አካል በአግባቡ እየሠራበት አለመሆኑን ሲያምንበትና ይህንንም በተግባር ሲያገጋግጥ ፍቃዱን ሊሠርዝ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት ፍቃድ ሊያሠርዙ የሚችሉ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ሙዚየሙን ያቋቋመው ሰው በራሱ ፍቃድ ፍቃዱን ሲመልስ
2. ሙዚየሙ ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር እየሠራ አለመሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣
3. የሙዚየሙ ቅርሶች ለአደጋ የተጋለጡ እንደሆነ፣ ሙዚየሙ ከፋይናንስ እጥረት፣ ከባለሙያ አለመኖር፣ ከደህንነት አኳያ ሊሠራ የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ፣
4. የሙዚየም ማቋቋሚያ ፍቃድ ከመሠረዙ በፊት ሙዚየሙን ያቋቋመው ሰው በማመልከቻ ሲጠይቅ ወይም የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ከቁጥር 1-4 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የሙዚየም ማቋቋሚያ ፍቃድ ከመሠረዙ በፊት ሊስተካከከል የማገባውና የሚቀጥልበት ሁኔታ ካለ ላቋቋመው አካል ለ1ወር የማስተካከያ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡
6. ሙዚየሙ የሚቀጥልበት ሁኔታ ካለ እንዲስተካከል ከባለስልጣኑ ሙያዊ ምክርና ድጋፍ ተሠጥቶ የማይስተካከል ከሆነ ማስጠንቀቂያ በጽሁፍ ተሰጥቶ ለአንድ ወር ይጠበቃል፡፡

7. ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ሁኔታዎች የማይስተካከሉ ከሆነ ፍቃዱ ይሰረዛል፡፡ ቅርሶቹም ህጋዊ በሆነ  መንገድ ወደ መንግሥት ይዞታነት ይዛወራሉ፡፡
8. ከባለሥልጣኑ እውቅና ውጭ በይዞታው ሥር የሚገኙ ቅርሶችን ለሌሎች ተመሳሳይ አካላት መተላለፉ በማስረጃ ከተረጋገጠ ፍቃዱ ያለ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ፍቃዱ ይሠረዛል፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 19. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውምሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሰራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 20. ቅጣት

ይህንን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

### 21. ስለተሻረ ህግ

ማንኛውም ይህንን መመሪያ የሚቃረን አሰራር ወይም ልምድ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

### 22. መመሪያውን ሰለማሻሻል

1. ይህን መመሪያአስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሚኒስትሩ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የሙዚየሞችን ወቅታዊ ሁኔታና የሥራ ሂደት በተመለከተ በሚቀርብለት ሪፖርትና በባለሙያዎች ምልከታ መሠረት ለቅርሶች አያያዝና አጠባበቅ ተገቢውን የሥራ መመሪያ ያወጣል፡፡ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

### 23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ________________ቀ___________________ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሚን አብዱልቃድር

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር

አዲስ አበባ